

# ኢየሱስና ሕፃናት

ኢየሱስ ሕፃናትን ይወዳል። ምንም እንኳን በጣም ቢደክመውም ሕፃናት ከአጠገቡ አይታጡም ነበር።

. አንድ ቀን በርከት ያሉ እናቶች ልጆቻቸውን እንዲባርክላቸው ወደ ኢየሱስ ይዘዋቸው መጡ። ደቀመዛሙርቱ ግን ኢየሱስ በጣም አገልግሎት ስለበዛበት በልጆቹ እንዳይጨናነቅ ልጆቹ ወደኢየሱስ እንዳይቀርቡ ተከለከሏቸው። ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ሕፃናቱን እንዳይለክሏቸው ካዘዛቸው በኋላ “ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።” አላቸው።

እጁንም በላያቸው አድርጎ ባረካቸው።

ይህ ታሪክ የሚገኘው በማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ 10፡13 – 16 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ነው።

http://gardenofpraise.com